# አይሰማው የለ ጆሮ

አዬ ጉዳችን ዘንድሮ
አይሰማው የለ ጆሮ
የሴትዮዋ ሲገርመን
ደበበ እሸቱ ደገመን::
አዬ ቃሊቲ
ስንቱን ጉድ ይዛ ኖሯል
ከእስረኛው ጋራ
ጉዱም አብሮ ተፈቷል::

ምነዋ የድሮው ጓድ
የዛሬው የቅንጅት ጉድ
በሎጎው ለመክበር
ወደ ዲሲ ሊነጉድ
ጠበቃ ሊገዛ
ገንዘብ ሊያገኝ
ብዙ ሺህ ዶላር ሲመኝ
ሎጎዬ ተሰረቀ ልከስ ነኝ
ብሎ ባደባባይ ሲናገር
እጅግ በጣም አሳቀኝ::

የልዑካን ቡድኑ ሚሽኑ
ገንዘብ ማግኘት ላይ መሆኑ
ሌላው ተልዕኮ ተረስቶ
እኔን ደነቀኝ ሚዛኑ::
እስቲ ሞክረው ይቅናህ
ጠበቃ ችግር ካለብህ
አይዞህ በርታ ለማለት
ፈጠነች አለችልህ::

የክሱ አርዕስት አጭር ነው
አዎን "ሎጎው የኔ ነው"
የኔ የደበበ ነው
በቃ አዎን የኔ ነው::

የሎጎው ባለንብረት ካለ
የማኒፌስቶው ይምጣ የት አለ
ጆሮ አይሰማው የለ
በገንዘብ ፍቅር እየነሆለለ
የቅንጅት ጉደኛ ጉድ
የሎጎው ባለቤት ተባለ::

ገንዘብ መውደዱ አልደነቀኝ
ሎጎው የቅንጅት መስሎኝ
የኔ ነው ሲል አሳቀኝ
ምነው መካሪ ቢያገኝ
ከልብ ካንጀቴ አሳቀኝ
ብዙ መቶ ሺህ ብር ካሳ ሊያገኝ
የካናዳው ልዑክ
ሲከብር ሲያልፍለት ታየኝ::